**የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም**

**የአዋጅ ቁጥር 1142/2011 ለማሻሻል የተዘጋጀ ማብራሪያ**

Excutive summary

***ታህሣሥ 2014 ዓ.ም***

***ማብራሪያ***

***መግቢያ***

***የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በህግ የተደነገጉ የሰዎች መብቶች በአስፈጻሚው አካል መከበራቸው በማረጋገጥ የህግ በላይነት መሠረት ያደረገ ጥራት፣ቅልጥፍና ግልጽነት ያለው መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን የማድረግ ዓላማን ለማረጋገጥ ተቋሙ በአፈፃፀም ሂደት በጥናት፣ቁጥጥር እና በምርመራ የተለዩትን የህግና የአሠራር ክፍተቶችን ለማረም በአንፃሩ ባከናወናቸው***

ሥራዎች ያዳበራቸውን አዎንታዊና ገንቢ ልምዶች ለመጠበቅና ይበልጥ ማጠናከር አስፈልጓል። በመሆኑም አሁን ስራ ላይ ያለውን አዋጅ ቁጥር 1142/2011ን በማሻሻል የዕንባ ጠባቂዎች አመራረጥ፣አሿሿም፣የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና የማዕከላት አደረጃጀት፣የሰራተኞች ቅጥርና አስተዳደር፣የተቋሙን ነፃነትና ገለልተኝነት በማረጋገጥ እንዲሁም አሁን ሀገሪቱ ከደረሰችበት የኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር የተቋሙን የመፈፀም አቅም በማስፋት በግል ድርጅቶች የሚፈጸሙ የአስተዳደር በደሎችን በመመርመር እርማት ለማካሄድ አዋጁን ማሻሻል በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ አቅርቧል።

**<u>ረቂቅ አዋጁን ለማዘጋጀት የተደረጉ ዝግጅቶች፡-</u>**

የተቋሙ ጉባኤ ሥራ ላይ የነበረውን አዋጁ ማሻሻል እንደሚያስፈልግ በመወሰን አንድ የባለሙያዎች ኮሚቴ በመመደብ የተለያዩ የጥናት፣የቁጥጥር፣የምርመራና ማስፈፀም ውጤቶችን፣የዕንባ ጠባቂ ጉባኤ ውሳኔዎችን፣ከሌሎች ተመሳሳይ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ተሞክሮ በመውሰድ እና አዋጅ ቁጥር 1142/2011 በማስፈፀም ሂደት የታዩትን ክፍተቶች በመፈተሽ ተቋሙ አሁን ለማምጣት ከሚፈልገው ለውጥ አንፃር ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ እንድሆን ያተዘጋጀውን ረቂቅ ሰነድ ለተቋሙ ጉባኤ፣በዋና መ/ቤት ለዳይሬክተሮች፣ለቅ/ጽ/ቤቶችና እና ለባለድርሻ አካለት በማቅረብ የተሰጣው ግብዓት ተካቶ ረቂቅ ሠነዱ ለተቋሙ ጉባኤ ቀርቦ አስተያየት የተሰጠበት የአዋጅ ቁጥር 1142/2011 ረቂቅ ማሻሻያ ለተከበረው ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከማብራሪያ ጋር አቅርበናል።

**በአዋጁ እንዲሻሻሉ የተፈለጉ ጉዳዮች**

1. የቅርንጫፍ እንባ ጠባቂዎች ከሹመት ይልቅ ሜሪትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ (አንቀጽ 12)
2. የተቋሙ ስልጣንና ተግባራት በመንግስት አስፈጻሚ አካላት እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚደርሰውን አስተዳደራዊ በደል ብቻ ተወስኖ የነበረው በትላልቅ የግል ተቋማት የሚደርሱ አስተዳዳራዊ በደሎችን መመርመር የሚየስችል ስልጣን ማከተት (አንቀጽ 7/3)
3. በኢትዮጵያ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 211/1142 ውስጥ ተካቶ የነበረው በተሳሳተ ትርጉም ከተቋሙ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1142/2011 ያልተካተተው የመርማሪ ባለሙያዎችና የእንባ ጠባቂዎች ያለመከሰስ መብት በድጋሚ ማከተት (አንቀጽ 38)
4. የሰራተኞችን ጥቅማ ጥቅም መወሰን በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮችን ለሚመለከተው የተከበረው ም/ቤት ከመስጠት ይልቅ በእንባ ጠባቂዎች ጉባኤ እንዲወሰን ማስቻል (አንቀጽ 12/3/መ)
5. የመገናኛ ብዙሀንና የመረጃ ነጻነት በክፍል ሶሰት የሚለው ሀረግ የመረጃ ነጻነት አዋጅ ተብሎ በአዋጁ ውስጥ እንዲሻሻል (አንቀጽ 7/11)

**በአዋጁ ላይ ማሻሸያ ለማድረግ ያስፈለጉ ምክንያቶች፡-**

1. **የቅርንጫፍ እንባ ጠባቂዎች ከሹመት ይልቅ ሜሪትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ**

በአዋጅ ቁጥር 1142/2011 የተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎችና የቅ/ጽ/ቤት ዕንባ ጠባቂዎች በም/ቤት ቀርበው እንዲሾሙ የሚያደርግ ሲሆን በመርህ ደረጃ እንደአስፈላጊነቱ የአገልግሎት አሰጣጥን ተደራሽ ለማድረግ በአንድ ክልል ከአንድ በላይ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ እና የክልላዊ የመንግስት አወቃቀርን መከተል የግድ ስለማይሆን የተከበረው የህዝብ ተወካች ም/ቤትም የእያንዳንዱን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንባ ጠባቂዎች በአዋጁ መሰረት ለመሾምና ለመሻር ከሚወስደው ጊዜ እንዲሁም ለተሿሚዎች የሚወጣውን ከፍተኛ ወጪ ለመቀነስ የቅርንጫፍ እንባ ጠባቂዎች በውድድር ሚሪትን መሰረት ባደረግ በእንባ ጠባቂዎች ጉባኤ እንዲሾሙ ማድረግ ለአሰራር ቅልጥፍና እና ውጤታማነት የተሻለ ሰለሚሆን በአንጻሩ የሃገራችን የኢኮኖሚ እና የዴሞክራሲያዊ እድገት መሰረት የዘርፍ እንባ ጠባቂዎች መሾም አስፈላጊ በሚሆንበት ሰአት ለመሾም እንዲቻል በቀጣይ በአጭር ጊዜ አዋጁን ማሻሻል ስለማይቻል በዚህ አዋጅ የተከበረው ም/ቤት አስፈላጊ የሆኑ የዘርፍ እንባ ጠባቂዎች እንደሚሾም ማከተት አስፈላጊ ስለሆነ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

2. **የተቋሙ ስልጣንና ተግባራት በመንግስት አስፈጻሚ አካላት እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚደርሰውን አስተዳደራዊ በደል መመርመር ብቻ ላይ ተወስኖ የነበረው  በትላልቅ የግል ተቋማት የሚደርሱ አስተዳዳራዊ በደሎችን መመርመር እንዲቻል የስልጣን ወሰኑን ማስፋት**

እስካሁን የኢትዮጵያ የህዝብ እንባ ጠበቂ ተቋም የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት በመንግስት አስፈጻሚ አካላት እና በመንግሰት ልማት ድርጅቶች የሚደርሱ አስተዳደራዊ በደሎችን እየተመለከተ የቆየ ሲሆን አሁን ሀገራችን ከምትከተለው የነጻ ገበያ ስርአት አንጻር ከመንግሰት ሚና ይልቅ የግል ተቋማት በኢኮኖሚው የሚኖራቸው ተሳትፎ እያደገ መምጣቱ የማይቀር በመሆኑ እና እስካሁን ወደ ተቋማችን ከሚመጡ አቤቱታዎች መካከል 52 % በተቋሙ ስልጣንና ተግባራት ወጪ ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ አብዛኛው በግል ተቋማት የደረሱ አስተዳደራዊ በደሎች የጎላ ድርሻ አላቸው ስለዚህ በቀጣይ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በግል ተቋማት የሚደርሱ አስተዳደራዊ በደሎችን መመልከት የሚያስችል የስልጣን ወሰኑን ማስፋት አስፈላጊ ስለሆነ፡፡

3. **ያለመከሰስ መብት** (Immunity)

በኢትዮጵያ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 211/1142 ውስጥ ተካቶ የነበረው ከተቋሙ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1142/2011 በተሳሳት ትርጉም ያልተካተተው የመርማሪ ባለሙያዎችና የእንባ ጠባቂዎች ያለመከሰስ መብት (Immunity) በድጋሚ ማከተት አስፈላጊ በመሆን በድጋሚ እንዲካተት ተደርጓል ምክንያቱም ልዩ መብት ለተሿሚዎች ከሆነ  በም/ቤቱ አፈ ጉባኤ እና የምርመራ ስራ ለሚያከናውኑ ዳይሬክተሮች ወይም  መርማሪ ባለሙያዎች ከሆነ ዋና ዕንባ ጠባቂው  ሳይፈቅድ ወይም ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እንጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር አይያዝም ፣አይከሰስም፣አይታሰርም ይህ መብት ለኢትዮጵያ የህዝብ እንባ ጠባቂዎች ብቻ የተፈቀደ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ በተባበሩት መንግስታት የእንባ ጠባቂዎች ሚና በፓሪስ መርህ በአፍሪካ ህብረት ቻርተር በኦሊበር ታምቦ ውጤታማ እንባ ጠባቂ በአውሮፓ ህብረት ካውንስል ወዘተ የአለም አቀፍ ድንጋጌዎች ውስጥ የእንባ ጠባቂ ተቋማት ነጻ እና ገለልተኛ ሆነው ስራቸውን ይሰሩ ዘንድ በህግ የተደገፈ ያለመከሰስ መብት እንደኖራቸው ይፈቅዳል ሆኖም ግን የቀደመው ም/ቤት ለእንባ ጠባቂዎች እና ለተቋሙ መርማሪዎች የሚፈቀደውን ያለመከሰስ መብት ለም/ቤቱ  አባላት ከሚሰጠው ህገ መንግስታዊ ያለመከሰስ መብት ጋር በማነጻጸር ከማሻሻያ አዋጁ በስህተት እንዲሰረዝ ተደርጓል ስለዚህ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለእንባ ጠባቂዎች እና መርማሪዎች የሚሰጠው ያለመከሰስ መብት ፈጽሞ ለም/ቤት አባላት ከሚሰጠው መብት ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑ ታወቀ በዚህ አዋጅ ውስጥ በድጋሚ እንዲካተት ተደርጓል በተመሳሳይ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ  መብቶች ኮሚሽነሮች እና መርማሪዎች የተሰጠ መብት ነው።

4. **የሰራተኞችን ጥቅማ ጥቅም መወሰን በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮችን ለሚመለከተው የተከበረው ም/ቤት ከመስጠት ይልቅ የእንባ ጠባቂዎች ጉባኤ እንዲወስን ማስቻል**

የተቋሙ ሰራተኞች የደመወዝ አስኬል በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በሚያወጣው ደንብ መሰረት  የሚወሰን ሲሆን የሰራተኞች ጥቅማ ጥቅም እና የትራንስፖርት አበል የሚወሰነው ተቋማት በሚያወጡት ደንብ መሰረት ይሆናል በዚህ መሰረት በአስፈጻሚ ስር ያሉም ሆኑ ለኢፌድሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተጠሪ ተቋማት በራሳቸው የሚወሰን ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሰራተኞች ጥቅማ ጥቅም በም/ቤቱ እንዲጸድቅ መደረጉ በዴሞክራሲ ተቋማት መካከል ሰራተኞች በሚያገኙት ጥቅማ ጥቅም ልዩነት በመፍጠሩ የፍትሀዊነት ጥያቄ አስነስቷል እንዲሁም በተቋሙችን ተጠንቶ ወደ ም/ቤት የተላከው የሰራተኞች ጥቅማ ጥቅም ከሶስት አመት በላይ በም/ቤቱ ሳይጸደቅ እስካሁን በመቆየቱ ለከፍተኛ የሰራተኛ ፍልሰት ምክንያት ሆኗል ለምሳሌ በተመሳሳይ መደብ ከተቋማችን በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወይም የፌደሬሽን ም/ቤት ሲቀጠሩ ይስተዋላል ስለዚህ የሰራተኞች ጥቅማ ጥቅምን ለመወሰን የእንባ ጠባቂዎች ጉባኤ ከአቻ ተቋማት እና ከሀገሪቷ አቅም አንጻር ባገናዘበ መልኩ መወሰን ስለሚችል የተቋሙ ሰራተኞች ጥቅማ ጥቅም በጉባኤ ማጽድቅ አስፈላጊ ስለሆነ ማሻሻል አስፈልጓል፤፤

5. **የመገናኛ ብዙሀንና የመረጃ ነጻነት በክፍል ሶስት የሚለው ሀረግ የመረጃ ነጻነት አዋጅ ተብሎ በአዋጁ ውስጥ እንዲሻሻል**

በነባሩ አዋጅ ቁጥር 1142/2011 የኢትዮጵያ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ክፍል ሶስት ተግባራዊ ስለመደረጉ የመከታተልና የመቆጣጠር ስልጣኝ የሰጠው ሲሆን በሪፎርሙ የመረጃ ነጻነት አዋጅ ተነጥሎ ራሱን ችሎ የወጣ አዋጅ በመሆኑ የኢትዮጵያ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የመረጃ ነጻነት አዋጅ ተግባራዊነትን ይከታተላል በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፤፤

በአጠቃላይ በሀገሪቱ እየሰፋ የመጣውን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ ተቋሙ  በአዳረጃጀቱ፣ነፃና ገልተኝነቱ፣የበጀት ምደባ ሥርዓቱን እና ሌሎችም ያቀረብናቸው የህግ ማሻሽያ ደንጋጌዎች  ፀድቀው ሥራ ላይ ከዋሉ ሌሎች የአሠራርና የውስጥ ችግሮቹን ተቋሙ እንድፈታ የተከበረው ም/ቤት ከህግ ማጽደቅ ጀምሮ የሚሰጠን ድጋፍ ለተቋሙ ጥንካሬ ተኪ ሚና የሌላው መሆኑን እንገልፃለን።